የሰ/መ/ቁ. 34076

ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ - ወኪል እስክንድር ወልዱ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው

2. ወ/ሮ አዳነች ወልዱ ፀጋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በውርስ ንብረት ክፍፍል ላይ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሳሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ስትሆን፣ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ላይ ድርሻዋን እንዲያካፍሉአት ነው፡፡ የውርስ ንብረት የተባሉት በአዲስ አበባ ከተማ እና በደሴ የሚገኙ ሁለት ቤቶች እንደሆኑም ተገልፆአል፡፡ ክሱ የቀረበለት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ወደ ክሱ ስረ ነገር ከመግባቱ በፊት አዲስ አበባ ከተማ ይገኛል በተባለው ቤት ላይ የዳኝነት ስልጣን የለኝም፣ ማስተናገድ የምችለው ደሴ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን ቤት በሚመለከት የሚቀርበውን ክስ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም የግዛት ክልል ስልጣን የለኝም በሚል በሚሰጥ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ

ሊቀርብ አይችልም፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሳያስተናግድ ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተወሰነው አመልካች ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበችው የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከተው ክስ በግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን ምክንያት አይስተናገድም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር መገዘብ እንደቻልነው አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የሟች አቶ ወልዱ ፀጋ ልጆች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የሟቹ ሚስት ናቸው፡፡ ሟች ይኖሩ የነበሩት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን እንደሆነና የሞቱትም በዚሁ ቦታ ስለመሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪዎች ሟች በኖሩበትና በሞቱበት  በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በደሴ ወረዳ ፍ/ቤት የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረባቸውን ከቀረበው ክርክር ተመልክተናል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተችው የውርስ ሃብት ነው ከተባለው ንብረት ላይ ድርሻዋን ለማግኘት ነው፡፡ በአጠቃላይ ክርክሩ የፍትሐብሔር እንደመሆኑ የሚመራው በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ሕግ መሰረት ነው፡፡ በግዛት ክልል ስለሚወሰን የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ በስነ- ስርዓት ሕጉ አንደኛ መጽሐፍ በምእራፍ 3 ስር ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ በቁ. 23 የተመለከተውም ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በውርስ ምክንያት የሚቀርብን ክስ የሚታይበትን ቦታ የሚወሰን ነው፡፡ ክሱ

መቅረብ ያለበት ወይም የሚቀርበው የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኘው ፍ/ቤት እንደሆነም ያመለክታል፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ የውርስ ሃብት የሆኑ ንብርቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚኖራቸው ጉዳይ እግምት ውጥስ የሚገባ አይደለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጽር ሲታይም የሕግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአማራ ብሔራዊ ክ/መ/ደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16355 ሰኔ 25 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1070/99 መስከረም 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ አይባልበትም የተባለው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ያረበችው የውርስ ክፍፍል ክስ መታየት ያለበት በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ክሱን በማስተናገድ በበኩሉ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡ ጉዳዩ ይመለስለት፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ